# Interest Free Banking Services

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
COMMERCIAL BANK OF ETHIOPIA

ሁሌም የሚተማመኑበት ባንክ!

# Interest Free Banking Services

**What do Interest Free Bnking Services (IFB) mean?**

- Interest free Bnking is a Bnking services that operates in line with islamic principles of business and finance;
- The services has its own operational standards
- The services accepts deposits and extends finance from and to permissible businesses respectively: and
- The IFB services is an all inclusive banking services that includes deposit, finance, money transfer and international trade services.

**How does the Commercial Bank of Ethiopia (CBE) provide the interest free banking services?**

- The CBE provides the services through windows dedicated for the IFB services only and has instituted mechanisms to ensure segregation of its interest free banking transaction from conventional banking services.

**Who are eligible for interest free Bnking Services?**

- Any individuals, business entities and governmental institutions fulfilling the eligibility criteria of the bank can use the services:

**What are the types of deposit services available under IFB?**

- **Wadia Amanah (Safe keeping deposit):** The Bank will not share benefit/losses on such accounts and deposit is returnable upon request.

- **Kerd (Demand Deposit):** This account is operated through the use of checks prepared for the same purpose. The Bank will not share benefit/losses on such accounts and deposit is returnable upon request.

- **Mudarabah Saving Deposit:** The Bank shares benefits/losses from its financing activities on such accounts. The deposit is returnable upon request;

- **Mudarabah Fixed Time Deposit:** The Bank shares benefits/losses that from its financing activities on such accounts. The deposit is placed for a fixed term. If customer(s) requests withdrawal before the contract period, he/she/it will forfeit or will not share the corresponding benefits/losses, as appropriate;

**What are the available financing types under IFB?**

- **Murabaha Financing:** It is a type of financing where the Bank expressly mentions the cost it has incurred on purchase of the Asset(s) and sells it to a customer, by adding some profit.

- **Istisna Financing:**

    - It is a mode of sale, at an agreed price, whereby the Bank places an order to manufacture, assemble or construct, or cause so to do anything to be delivered at a future date;

- Istisna financing is a mode of sale/ transaction where a commodity is transacted before it is manufactured. It is an order to a manufacturer to manufacture a specific commodity for a purchaser/customer of the bank. The manufacturer uses its/his/her own material to manufacture the required goods. In this mode of financing, price must be fixed with consent of all parties involved.

- **Salam Financing**

  - The seller/customer undertakes to supply specific goods to the Bank at a future date in exchange of an advance price fully paid at spot, but the supply of purchased goods is differed to a fixed date;

  - The seller/customer gets in advance the money he/she/it wants in exchange for his/her/its obligation to deliver the commodity later;

- The Bank buys the farm output to be produced in the future against the full spot payment of the price which may be utilized by the farmer to meet his/her/its financing needs.

**What are the available international trade services under IFB?**

- The Interest free banking services window provides a wide array of international trade services that mainly includes letter of credit, guarantee, international money transfer services and foreign exchange services.

**Commercial Bank of Ethiopia**

**The bank you can always rely on**

# ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

## ባንኩ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎትን እንዴት ይሰጣል?

- በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተሰራባቸው ያሉ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት አሰራር መርሆችን በመከተል፡፡
- ለዚሁ ሥራ በተለዩ የአገልግሎት መስኮቶች አማካኝነት ደንበኞችን በማስተናገድ፡፡
- ከወለድ ጋር ከተያያዙ የባንክ አገልግሎቶች የተለየ እንዲሆን የሚያስችል አስተማማኝ የውስጥ አሰራር በመዘርጋት፡፡

## ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎቶችን መጠቀም የሚችለው ማን ነው?

የእያንዳንዱን የአገልግሎት ዓይነት መስፈርት የሚያሟሉ የሚከተሉት አካላት ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ፡፡

- ግለሰቦች
- ድርጅቶች እና
- መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

## ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት ምን ዓይነት የባንክ አገልግሎቶችን ያካትታል?

✓ የተቀማጭ ገንዘብ፣

- ✓ የንግድ ሥራ አጋርነት፣
- ✓ የዓለምአቀፍ ንግድ ድጋፍ አገልግሎቶች፣
- ✓ የገንዘብ ዝውውር/ማስተላለፍ እንዲሁም
- ✓ የውጪ ምንዛሬ አገልግሎቶች ይገኙበታል፡፡

## የተቀማጭ ገንዘብ አገልግሎት ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?

- የአደራ ተቀማጭ ገንዘብ ሂሳብ (ዋዲያሕ-አማናህ)
  - ✓ ይህ የተቀማጭ ገንዘብ ዓይነት ላልተወሰነ ጊዜ ያለ ትርፍ ክፍያ በአደራ የሚቀመጥ ነው፡፡
  - ✓ የገንዘብ ምንጩ ከተፈቀዱ የሥራ መስኮች መሆን ይኖርበታል ፣
  - ✓ ባንኩ ገንዘቡን በተጠየቀ ጊዜ ለባለቤቱ ይከፍላል ፣

- **የተንቀሣቃሽ ገንዘብ ሂሳብ (ቀርድ)**
  - ✓ ይህ ሂሳብ በሚመለከታቸው አካላት ተከፍቶ ላልተወሰነ ጊዜ የሚቆይ፣ ያለገደብ በቼክ አማካይነት የሚንቀሳቀስ ነው ፣
  - ✓ ትርፍ/ኪሳራ አካፋይ አይደለም፤ ሆኖም ባንኩ በራሱ ፍላጎት እንደሁኔታው እያየ ለአስቀማጮች የማበረታቻ ስጦታ ሊያደርግ ይችላል፣

- ✓ የገንዘብ ምንጩ ከተፈቀዱ የሥራ መስኮች መሆን አለበት፤
- ✓ ባንኩ በተጠየቀ ጊዜ ለባለቤቱ ወይም ላዘዘለት ይከፍላል፤

- **ትርፍ/ኪሳራ አካፋይ ተቀማጭ ገንዘብ (ሙዳራባሃ)**
  - ለትርፍ/ኪሳራ ተካፋይነት ላልተወሰነ የጊዜ ገደብ የሚቀመጥ ነው ፤
  - የገንዘብ ምንጩ ከተፈቀዱ የሥራ መስኮች መሆን አለበት ፤
  - ደንበኛው በማንኛውም ወቅት ሂሳቡን መዝጋት ይችላል፤ ሆኖም ትርፍ/ኪሳራ የሚጋራበት እንደመሆኑ መጠን ባንኩ መለስተኛ ወጪ የማድረግ ገደቦችን ሊጠቀም ይችላል፤

- **ትርፍ/ ኪሳራ አካፋይ በጊዜ ገደብ የኢንቨስትመንት ተቀማጭ (ሙዳራባ መርሕ)**
  - ✓ ለትርፍ /ኪሳራ ተካፋይነት ለተወሰነ የጊዜ ገደብ የሚቀመጥ ነው፤
  - ✓ የገንዘብ ምንጩ ከተፈቀዱ የሥራ መስኮች መሆን አለበት ፤
  - ✓ በውል ከተመለከተው የጊዜ ገደብ ውጪ በማንኛውም ጊዜ ገንዘቡ በባለቤቱ ወጪ የሚደረግ አይሆንም ሆኖም በውል

ከተወሰነው ጊዜ በፊት ባለገንዘቡ እንዲከፈለው ከጠየቀ ትርፍ ላይከፈለው ይችላል፣

✓ ባንኩ ገንዘቡን ለማንኛውም ዓይነት "የተፈቀደ" የኢንቨስትመንት ሥራ ዓይነት ይጠቀምበታል።

## የንግድ ሥራ አጋርነት አገልግሎት ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው?

- ### ለንግድ ሥራ ማስኬጃ እና ለቋሚ እቃዎች መግዣ የሚውል የዱቤ ሽያጭ (ሙራባሃ ኮንትራት)

በአገር ውስጥም ሆነ በላኪነት የንግድ ሥራ የተሠማሩ ነጋዴዎች ለንግድ ሥራቸው የሚያስፈልጉዋቸውን ግብዓቶች በመለየት እና ዋጋ በማጥናት፤ የሚገዙበትን ዋጋ፣ ሊከፍሉ የሚችሉትን የትርፍ መጠን፣ የመክፈያ ጊዜውን፣ ዋስትና የሚያስፈልገው ከሆነ ዋስትናቸውን በመግለጽ፤ ባንኩ እንዲሸጥላቸው በመጠየቅ ከባንኩ ወኪል ወይም ከባንኩ በዱቤ በመግዛት የሽያጩን ገንዘብ እና ስምምነት የተደረሰበትን ትርፍ በውል በሚወሰን ጊዜ ውስጥ ከፍለው የሚጨርሱበት አሠራር ነው። ቋሚ ንብረት በመግዛት ለመጠቀምም ሆነ መልሶ ለመሸጥ የሚፈልጉም ከላይ በተገለጸው ሁኔታ በመጠቀም ከትርፍ ጋር ይከፍላሉ። በተጨማሪም ባንኩ በውክልና የውጪ አገር ንግድ ሥራዎችን እንዲያከናውንላቸው ለሚፈልጉ የአገልገሎት ክፍያ ወይም ትርፍ በመክፈል በተፈቀዱ እና በተመረጡ መስኮች ላይ መሥራት ይቻላል።

- የእርሻ ቅድመ -ምርት - ሽያጭ ውል (ሰላም ኮንትራት)

በገበያ የታወቁ ምርቶችን የማምረት እርሻ ሥራ ላይ የተሠማሩ አካላት ከእርሻው ምርትን ለማምረት የሚያስፈልጉትን ወጪዎች ለመሸፈን የሚጎድላቸውን ገንዘብ ለማሟላት የቅድመ-ምርት ሽያጭ ውል ከባንኩ ጋር በመዋዋል እና የሚመረተውን ምርት የሚገዛቸውን አካል በማዘጋጀት ከባንኩ ጋር በተመሳሳይ ምርት ላይ ቅድመ-ምርት-ግዢ ስምምነት ከለላ ገዢ ጋር በተደረገ ጊዜ ባንኩ የሸያጩን ገንዘብ በቅድሚያ ምርቱን እንዲያመርቱበት ይከፍላቸዋል፤ ምርቱ በደረሰ ጊዜ ለባንኩ ወይንም ለወኪሉ ወይም ከባንኩ ጋር ቅድመ-ምርት-ግዢ ስምምነት ላደረገ አካል ምርቱን በማስረከብ በቅድመ ክፍያ የወሰዱትን ገንዘብ በውሉ ላይ በተጠቀሰው ዝርያ ዓይነት፤ መጠን፤ ቦታ፣ጥራት፤እና ዋጋ መሠረት በማቅረብ እዳውን ይከፍላሉ።

- ለሚገነቡ ወይም ለሚፈበረኩ ንብረቶች የዱቤ ሽያጭ ውል (ኢስትሲና ኮንትራት)

በፋብሪካ የሚመረቱ፣ ወይም የሚገጣጠሙ ምርቶችን እና ተገንብተው የሚሸጡ ንብረቶችን ለመግዛት የሚፈልጉ እና መስፈርት የሚያሟሉ ደንበኞች ንብረቶቹን ከባንኩ ላይ ለመግዛት ቅድመ ግዢ ስምምነት ይፈፅማሉ፤ ባንኩ በምርት ወይም በግንባታ ሂደት ላይ ያሉ ንብረቶችን ለመግዛት ከፋብሪካው ወይም ከገንቢው በመዋዋል ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገውን ወጪ በግዢ ክፍያ መልክ ለፋብሪካው ወይም ለገንቢው በየእርከኑ በመክፈል ምርቱ ወይም ግንባታው ሲጠናቀቅ

አስቀድመው የግዢ ስምምነት ላደረጉ ደንበኞች በማስተላለፍ የገዙበትን ዋጋ በውል በሚወሰነው አከፋፈል ሁኔታ እና ጊዜ ውስጥ የሚከፈልበት አሠራር ነው። በሌላ በኩል ባንኩ ደንበኞቹ የሚፈልጉትን የንብረት ዓይነት እንዳቀረበላቸው እና እንደተረከቡ ክፍያ ሙሉ ለሙሉ ከፍለው ለመረከብ የቅድመ-ሽያጭ-ውል-ከተዋዋሉ በኋላ ባንኩ ያንን ዓይነት ንብረት የሚያመርትለትን ወይም የሚገነባለትን ባለሙያ በማፈላለግ ካስመረተ ወይም ካስገነባ በኋላ የግዢ ሥምምነት ላደረጉ ደንበኞች የሚያስረክብበትን አሠራርም ሊከተል ይችላል።

## ምን ዓይነት የዓለም አቀፍ ንግድ ድጋፍ አገልግሎቶችን ያገኛሉ?

ማንኛውንም የውጭ ንግድ አገልግሎት ማለትም፡- አስመጪዎች ለሚገዟቸው እቃዎች ለሻጭ (ላኪ) የክፍያ ዋስትና የመስጠት፣ ለዓለም አቀፍ ንግድ የውል ማስከበሪያ እና የሥራ አፈፃፀም ዋስትና መስጠት፣ በላኪ እና አስመጪ መካከል ለሚፈፀም የቅድመ-ክፍያ ዋስትና የመስጠት፣ ክፍያዎችን በውጭ ምንዛሪ መክፈል፣ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ዝውውር አገልግሎት መስጠት፣ የተላከ እቃን ሰነድ መግዛት፣ ከላኪዎች የሚላኩ ሰነዶችን ተረክቦ ለአስመጪዎች ማስረከብ፣ የውጪ ምንዛሪ አገልግሎት፣ የመርከብ አጓጓዦች ዋስትና እና ሌሎችንም የዓለም አቀፍ ንግድ ድጋፍ አገልግሎቶችን ይሰጣል። ሆኖም ከአገልግሎቱ ተጠቃሚ ደንበኞች ጋር ቅድመ-ሥምምነት መፈጸም ያስፈልጋል።

- ✓ ባንኩ በሚሰጠው የዓለም አቀፍ  ንግድ አገልግሎት የደንበኛው ወኪል ሆኖ በውክልና (ወከላሕ) ወይም በዱቤ ክፍያ /ሙራባሃ/ መርሕ ወይም በተለያየ እርከን ሁለቱንም መርሆች ሊከተል ይችላል፣

- ✓ የደምበኞች ወኪል ሆኖ አገልግሎት ሲሰጥ በቅድመ ስምምነት መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ወይም ኮሚሽን ይሰበስባል፣

- ✓ በዱቤ ክፍያ ወይም በሙራባሃ መርሕ የሚሰጡ የውጪ ንግድ አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ ባንኩ ለገቢ እቃዎች ግዢ የሚፈፅመውን ገንዘብ ደንበኞች በቅድመ ሥምምነት መሠረት የተስማሙበትን የትርፍ ክፍያ ጨምረው በአንድ ጊዜ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይከፍላሉ።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
COMMERCIAL BANK OF ETHIOPIA

**Interest Free Banking Services**

Tel: 251-11-551-50-04
251-11-551-24-52
Fax: 251-11-551-21-66
P.O.Box: 255
E-mail: cbecomu@combanketh.et
SWIFT CODE: CBETETAA
Website: www.combanketh.et